

# የትንቢት ቃል

አራተኛ ዓመት, ቁጥር 2

ሰኔ 2002

## «ከሰማይ የወደቀው መልአክ»

ይህች ምድር ስለምን በክፋት ተሞላች? የሰው ልጆች ስለምን በጦርነት እርስ በርሳቸው ይጨራረሳሉ? በየእለቱ ስለምን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በበሽታ፣በረሃብና በስቃይ ያልቃሉ? ስለምን ሐሰትና ተንኮል በዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው በእውነትና በጽድቅ ላይ ያፌዛሉ? ምንም ያልበደሉ የሕጻናት እሮሮ እስከ መቼ ድረስ ይሰማል? የመላው ተፈጥሮ የዋይታ ድምጽስ ምክንያቱ ምንድን ነው? ጥያቄ ጥያቄ ጥያቄ ...

ስለምን? እስከመቼ? እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ያላቀረበ ሰው የለም። ይህ «ከሰማይ የወደቀው መልአክ» በሚል ርእስ ያቀረብኩት መልእክት ለጥያቄዎቻችን በሙሉ መልስ ይሆናል በማለት ሳይሆን የክፋትና የጥፋት መጀመሪያው የት እንደሆነና መጨረሻው ደግሞ ምን እንደሚመስል የዘመናት መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ) የሚነግረንን ከሞላ ጎደል አብረን እንድንመለከት ነው።

በተጨማሪም የዚህ መልእክት ሌላ አላማ በአሁኑ ጊዜ በክርስቶስና በሰይጣን፣በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለው ጦርነት እየተባባሰና ወደ መጨረሻው እየደረሰ እንደሆነ ለማስገንዘብ ሲሆን፤እያንዳንዱ ግለሰብም በዚህ ታላቁ ተጋድሎ ውስጥ ከማን ጎን እንደሚሆን ዛሬውኑ መወሰን እንዳለበት ለማሳሰብ ነው። በዚህ ውሳኔ መሠረትም የአንድ ሰው የዘላለም ድርሻ ምን እንደሆነ ይታወቃል።

እግዚአብሔር የሚፈጥረው ሁሉ ንጹህና መልካም ነው። በዘፍጥረት 1፥31 ላይ «እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበር» ይላል። ትእቢት ወደ ሉሲፈር ልብ እስከገባበት ጊዜ ድረስ ሰማይ የደስታና የሰላም ቦታ ነበር። ኃጢያት የሚባል ነገርም አይታወቅም ነበር። ሉሲፈር ግን ከትእቢቱ የተነሳ በፈጣሪው ላይ አመጸ። ይህም የኃጢያት መጀመሪያ ሆነ «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥እንዴት እስከምድር ድረስ ተቆረጥህ? አንተም በልብህ «ወደ ሰማይ አርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ከደመናዎችም ከፍታ በላይ አርጋለሁ በልዑል ም እመሰላለሁ አልህ» (ኢሳ 14፣12-14)። «በውበትህ ምክንያት ልብህ ኮርቶአል። ከክብርህ የተነሳ ጥበብህን አረከስክ። በምድር ላይ ጣለሁህ፣ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት ሰጠሁህ» (ሕዝ 28፣17)።



ከዚህ አይነቱ የትእቢት አመጻ የተነሳ በሰማይ ጦርነት ሆነ ይለናል መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በሰማይ ሰልፍ ሆነ፥ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም፥ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም። አለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀድሞው አባብ ተጣለ፥ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ» (ራእይ 12፣7-9)። የሱስም ስለዚህ ነጥብ ሲናገር «ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» አለ (ሉቃ 10፥18)።

«ኃጢያትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢያትን ያደርጋልና» (1ዮሐ 3፥8)። የጥንቱ ሉሲፈር በእግዚአብሔር ላይ ያሳመጻቸውን አንድ ሶስተኛ መላእክት ይዞ ወደዚህች ምድር ተጣለ። እነዚህ እርኩሳን መናፍስት እግሮቻቸው ስቃይንና ሞትን ለማምጣት ይፈጥናሉ። ዛሬ አጋንንት የሙታንን ምስል በመውሰድ በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎችን ያስታሉ። «ሙታን በእውነት አልሞቱም፣ከፍ ባለ ቦታ ላይ ደስተኞች ሆነው እየኖሩ ነው» በማለት ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነ ሐሳዌ ትምህርታቸውን እያስፋፉ ሰዎች በምድር ሕይወታቸው ጊዜ ስለ ደህንነት ጥያቄ ብዙ እንዳያሰላስሉ ያደርጋሉ። በትምህርታቸውም ሰው ከሞት በኋላ ሌላ እድል እንዳለው አድርገው ያቀርባሉ።

ሰይጣን ወደ ምድር ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ አመጻውን እንደቀጠለ ነው። እግዚአብሔር እጅግ መልካም አድርጎ በፈጠረው ተፈጥሮ ውስጥም እጁን በማስገባት የመጀመሪያዎቹን ሰዎች

*(በገጽ 3 ይቀጥላል)*

## የሃያ ሚሊዮን ዶላሩ ሽርሽር

እድሜዬ የ5 አመት እያለ ነበር አንድ ቀን ወደ ጠፈር እበራለሁ ብዬ የወሰንኩት። እነሆ ዛሬ ይህ ሕልም እውን ሆነልኝ» በማለት ነበር የደቡብ አፍሪቃዊው ማርክ ሻትልወርዝ የጠፈር ጉዞውን የጀመረው።

በጠፈር ጉዞ ታሪክ ውስጥ ከአሜሪካዊው ዴኒስ ቲቶ ቀጥሎ ማርክ ሁለተኛው ቱሪስት ሲሆን ለዚህ 11 ቀናት የጠፈር ሽርሽር 20 ሚሊዮን ዶላር ነበር የከፈለው። የዚህ የ28 አመት ወጣት ነጋዴ የጠፈር ቆይታ በተለይ በደቡብ አፍሪቃ ታላቅ አድናቆትን በማትረፉ የአገሩ ሰዎች «Space Hero» (የጠፈሩ ጀግና) የሚል ቅጽል ስም ሰጥተውታል።

ውድ አንባቢ ሆይ፥ ይህንን በሚያዝያ 25 2002 በመላ አለም የተሰራጨውን ዜና እርስዎም ሳይከታተሉ የቀሩ አይመስለኝም። ለመሆኑ ይህንን ዜና በሰሙ ጊዜ በልብዎ ምን አይነት ስሜት ተቀስቅሶ ይሆን? አስደነቀዎት? አስገረመዎት? ወይስ «ይህ ምን አይነት ብኩን ሰው ነው! ገንዘቡን ለድሆች ቢሰጥ አይሻልም ነበር?» አሉ።

እኔ ይህንን ዜና ስሰማ በመጀመሪያ ደረጃ በጣም ተደነቅሁኝ። የማርክ ምኞት የኔም ምኞት ስለነበር። እኔም በልጅነቴ አስትሮናውት የመሆን ፍላጎት ነበረኝ።

*(በገጽ 6 ይቀጥላል)*

በዚህ እትም ውስጥ

| | |
|---|---|
| «ከሰማይ የወደቀው መልአክ» | 1 |
| የሃያ ሚሊዮን ዶላሩ ሽርሽር | 1 |
| ከአዘጋጆች | 2 |
| ኤልሮኢ | 2 |
| ከአንባቢዎች | 2 |
| «ሶስት ሰዎች የሚሰብኩባትን ቤተክርስቲያን ፈልግ!» | 3 |
| የጎመን የፈውስ ኃይል | 4 |
| ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት - ክፍል 3 | 5 |
| የተስፋፋው ተቃርኖ - ክፍል 2 | 6 |
| «የበረሃ ሕይወቴ ለመለመች» | 7 |
| ማስታወቂያዎች | 7 |
| የጥያቄዎ መልስ | 8 |

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ከአዘጋጆች  ወንጌል

## ኤልሮኢ

*የተወደዱ አንባቢ ሆይ!*

በአለማችን ውስጥ በታላቅ ፍጥነት የሚፈጸሙትን ክስተቶች በአተኩሮ የሚከታተል ሰው የምንኖርበት የታሪክ ጊዜ በጣም የተለየ እንደሆነ ይረዳል። በብርሃንና በጨለማ፣በእውነትና በሐሰት፣በጽድቅና በኃጢያት ማለትም በክርስቶስና በሰይጣን መሐከል የሚደረገው ፍልሚያ እየተባባሰና ወደ መጨረሻው እየመጣ ነው።

በዚህ በታላቁ ተጋድሎ መሐል «እኔ ጎን አልይዝም» ማለት አይቻልም። ወይ ከብርሃን ጋር ነን ወይንም ከጨለማ? ወይ በእውነት ታጥቀናል ወይንም በሐሰት ተውጠናል? ወይ የየሱስን ጽድቅ ለብሰናል ወይንም በኃጢያት ተበክለናል። ወይ የክርስቶስ ልጆች ሁነናል ወይንም ሰይጣን ባሪያዎቹ አድርጎናል?

ጊዜው ከእንቅልፍ የምንነሳበት የምርጫና የውሳኔ ጊዜ ነው። ጊዜው ውሳኔአችንን በየእለቱ የምናጸናበትና በትጋት የምንኖርበት ነው። ጊዜው የምድርን ተድላና ምቾት የምናሳድድበትና መዝገባችንን በዚህች አለም የምንሰበስብበት ሳይሆን ሊመጣ ያለውን የሰማይ ንጉሥ በጉጉት የምንጠብቅበት ነው። ጊዜው ነፍሳት ከሰይጣን ወጥመድና ከዘላለም ሞት እንዲተርፉ ብለን የሶስቱን መላእክት ዜና (ራእይ 14፥6-12) በታላቅ ድምጽ የምናሰራጭበት ከእንቅልፍ የምንነሳበት ነው። ጊዜው አምላካችንን ለመገናኘት የምንዘጋጅበት ነው።

በዚህች እትም ውስጥ ያሉት መልእክቶች በታላቁ ተጋድሎ ውስጥ በሚያደርጉት የየእለት ውሳኔዎ ስለኃጢያትዎ ብሎ በሞተው ጌታ ጎን እንዲቆሙ ማበረታቻ እንደሚሆኑ እናምናለን።

*የናንተው፥*
*ዳዊት መሐሪ እና ዳዊት መንግሥቱ*

ኤልሻዳይ፣ኤልሻዳይ፣ኤልሻዳይ
የምመካብህ ሁሉን ቻይ።
ሳዝን የምትደርስልኝ
ስፈራ የምታጽናናኝ።
የተሰነቀልኝ የሰው ስንቅ፣
ጉዞዬን ሳልጨርሰው ሲያልቅ።
የምታነሳኝ ከወደቅሁበት
ግራ ስታጋባኝ ሕይወት።

ልፋቴን ተስፋ መቁረጤን፣
ተመልክተህ የበረሃ ውሎዬን።
መንገዱ ጠፍቶብኝ ስሰደድ፣
እንባዬ ሲወርድ።
አባባ! አንተ አኮ ነህ ጋሻ የሆንከኝ፣
በውሃው ምንጭ አጠገብ ፈልገህ ያገኘኸኝ።

ሮጬ ሮጬ ሲለኝ ድክም፣
ሁሉም ጨልሞብኝ ተዘግቶ በሩም፣
እንቆቅልሼን ማን ሊፈታው?
ብዬ ሳልጨርሰው፣
አበዛልኝ ትእግሥት ቸርነቱን
ሰጠኝ እንደገና ሰላምን።

ኢየሱስ ነው የረዳኝ፣
በፍቅር አይኖቹ የተከተለኝ፣
የራራልኝ ያልተወኝ፣
ያልፈረደብኝ የተቀበለኝ፣
የሞላው ማድጋዬን፣ያጠፋው ችግሬን።
ዛሬንም የሚያየኝ ያየኝ፣
ወደፊትም የሚመራኝ።
የማያልቀው የመካን ታሪኬን፣
ልሰማው ሊተርክልኝ፣
የቅዱሳንን ሃገር ሊያወርሰኝ።
ጊዜው ተቃርቧል፣
ክብሩ ሊገለጽ በኃይል።
እናፍቃለሁ ያቺን ቀን፣
ኤልሮኢ ብዬ ያልኩትን፣
ላገኘው ጌታዬን፣ላገኘው ጌታዬን።

*አይናለም ከተማ, ከጀርመን*

# ከአንባቢዎች

ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች, የጌታ የየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።
አምላካችን እግዚአብሔር በሰጣችሁ ጊዜና ሰአት፣አንድነትና ብርታት ጸጋ መጽሔታችሁ ብዙ አላዋቂዎችን አዋቂዎች አድርጎአል። ብዙ የእውነትን ቃል ረሐብተኞችን አጥግቦአል። ለወደፊቱም ቢሆን እግዚአብሔር አምላካችን ለራሱ ክብር መልካሙን ሥራ በእናንተ በልጆቹ የጀመረው እስከምጽአት ድረስ እንደሚፈጽመው እምነቴ ነው።
ጌታ አስፍቶአችሁ የያዛችሁትን የእውነት ቃል ከተራራ ላይ ሆና እንደምትታይ ብርሃን እንድትሆኑ ያበቃችሁ ዘንድ ለእናንተ አገልግሎት በጸሎት እተጋለሁ። በመጨረሻም የመጽሔታችሁ አቀራረብ መስህብነት ያለው ስለሆነ እጅግ የሚጠቅምና የእውነትን ቃል ለይተን እንድናገናዝብ ይረዳልና በርቱ። ጌታ ይባርካችሁ ቀጥሉበት እላለሁ።

*መምህር ታዬ አበራ ለማ, ከ ጋምጎፋ*

ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች፥ የክርስቶስ ጸጋና ኃይል ዘወትር ከናንተ ጋር እንዲሆን እመኛለሁ። በየሶስት ወሩ የምትወጣውን የሚባርክ ጽሁፍ የያዘችውን መጽሔታችሁን በእጄ ሳገኘው እጅግ ተደስቼአለሁ። ወደ ጌታ ቃል የሚያቀርብና የሚያስተምር የሚያጽናና መልእክት አለበት። ጌታ ይባርካችሁ። ለተቀደሰው ተግባራችሁ እኔም በጸሎቴ አስባችኋለሁ።

*አዲስ ከተማ, ከኢንግላንድ*

ለትንቢት ቃል አዘጋጆች! ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። በትንቢት ቃል መጽሔት አማካኝነት ምስጋናዬን በውጭ አገር የሚኖሩትን ወገኖች ላመሰግን እወዳለሁ። ምክንያቱም «በልቶ ጠጥቶ ዝም የጋን ወንድም» ይባላል። የአበላ አድቬ/ክ ለብዙ ጊዜ የሙዚቃ መሳሪያ ለመግዛት ምኞትና ጉጉት ቢኖራትም ለመግዛት ስላልቻለች በእስራኤል አገር ለሚገኙት አድቬንቲስት ወገኖች የተቻላቸውን እንዲረዱን ጠይቀናቸው ነበር። እነርሱም በቀና መንፈስ የተቻላቸውን በአቶ ጌጡ ካሳ አስተባባሪነት ገንዘብ ልከውልን አንድ የራሺያ አኮርዴዮን ገዝተን ይኸውና ቤ/ክ ጌታን በሙዚቃ መሳሪያም እያመሰገነች ትገኛለች። ታዲያ እኛም የጋን ወንድም መሆን አንፈልግምና እጃቸውን ለዘረጉልን ወገኖች በሙሉ ከልብ አመስግነናል፣እግዚአብሔር ይመስገን። በተለይ ደግሞ ስሟእዲጠቀስ ያልፈለገች እንዲሁ በውጪ አገር የምትኖር እህት በላከችልን የገንዘብ እርዳታ የኳየር መዘምራን አዲስ የደንብ ልብስ እንድንለብስ በቅተናል።
ለዚህም የአበላ አድቬ/ክ ምስጋናዋን ታቀርባለች።

*ወንጌላዊ ባህሩ ባዩህ, ከአበላ*


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# «ሶስት ሰዎች የሚሰብኩባትን ቤተክርስቲያን ፈልግ!»

## ወንጌል በኢትዮጵያ



በኢትዮጵያ የሰባተኛ ቀን አክባሪ አድቬንቲስት ቤ/ክ ታሪክን በተመለከተ የትንቢት ቃል መጽሔታችን በመጋቢት 2001 እትምዋ ላይ ባቀረበችው ከአድቬንቲስት ሪቪው መጽሔት በተተረጎመው ጽሑፍ ላይ ጥቃቅን ስህተቶች መኖራቸውን አንዳንድ አንባቢዎች ጠቁመውን ነበር። ይህንን ነጥብ ፓስተር ጥሩነህ ወ/ሥላሴ የቀድሞው የኢትዮጵያን ዩኒየን ፕሬዚደንት ግልጽ እንዲያደርጉልን ከዚያም ባሻገር ደግሞ በኢትዮጵያ የቤተክርስቲያናችንን ታሪክ አጠር ባለ መልኩ እንዲያስቀምጡልን ጠይቀናቸው ነበር። የሰጡንን መልስ አብረን እንቋደስ፥

የአድቬንቲስት ሪቪው በዲሴምበር 14, 2000 ባወጣው እትሙ ዶ/ር ሮጀር ኩን ስለ ሽህ ዘካሪያስና ስለ አድቬንቲስት ሥራ አጀማመር በሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ የጻፈውን ተመልክቼ ስህተት እንዳለበት ስለተገነዘብኩ ለአሳታሚዎቹ ገልጬ ጽፌላቸው ነበር። ግን እስካሁን መልስ አላገኘሁም። እርማት ወይም ማስተካከያ ቢያደርጉ መልካም ነበር። እናንተም ጽሑፉን ስትመለከቱ የጎመጀችሁ ይመስላል ወዲያው በ «ትንቢት ቃል» መጽሔታችሁ ላይ ትርጉሙን ስላወጣችሁት ባለፈው አመት በጀርመን አገር በነበርኩ ጊዜ ተመልክቼዋለሁ። አሁን ግን ስህተት አለበት ካልህ በል አንተው ትክክሉን ተናገር ያለችሁ ይመስላል። ስህተቱን በማረም ከዚያም ባሻገር ትክክለኛን የቤተክርስቲያናችንን ታሪክ አጠር አድርገህ ጻፍልን ብላችኋል። የቤተክርስቲያንዋን ታሪክ በዚች ላይ አጠር አድርጎ ማቅረቡ እንኳን ዘበት ነው። ግን ትንሽ ከላይ ስለተጠቀሰው ዶክተር ኩን ስለጻፈው በመጠኑ ልናገር፥

መጀመሪያ ስህተቶቹ፥

1ኛ የአለቃ ዘካሪያስ አማች አለቃ ሞትባይኖር አይደሉም የእርሳቸው አማች አለቃ ገብረእግዚአብሔር ይባሉ ነበር። አለቃ ገብረእግዚአብሔርም ከአለቃ ዘካሪያስ ተማሮች አንዱ ነበሩ።

2ኛ ከመጀመሪያው ስህተት የሚመነጩ ሌሎች ስህተቶችም አሉ። አለቃ ዘካሪያስ ለአለቃ ሞትባይኖር የሰጧቸው አደራ የተባለው ስህተት ነው። አደራው የተሰጠው ለአለቃ ሞትባይኖር በግል ብቻ ሳይሆን ለመላው ተማሮቻቸው ነበር። የርሳቸውን አደራ ተከትለው ለመፈጸም ሲሞክሩ እስራት የደረሰባቸው አለቃ ሞትባይኖር ብቻ ሳይሆን በሙሉ ተማሮቻቸው ነበሩ። ከመጀመሪያው ስህተት የመነጩ ሌሎች ስህተቶች በመጣጥፉ ውስጥ በርከት ያሉ ስለሆነ ሁሉንም በዚህ ላይ መዘርዘሩ አስፈላጊ አልመሰለኝም። የሚያዋጣው መጣጥፉ ታርሞ እንደገና ቢጻፍ ነው።



«ሶስት ሰዎች የሚሰብኩባትን ቤተክርስቲያን ፈልግ!»

ሶስቱን ሰዎች በተመለከተ የተጻፈውም ስህተት አለበት። ትክክለኛው ገጽታ እንዲህ ነበር፥

አለቃ ዘካሪያስ ከእስልምና ተመልሰው ክርስትናን ተቀብለው በሚጠመቁበት ጊዜ አንድ የተከሰተ ችግር ነበር። ይከውም ከተማሪዎቻቸው ገሚሶቹ በአማቻቸው በአለቃ ገብረእግዚአብሔር መሪነት በዚህ መልኩ አንጠመቅም ብለው አስቸግረዋቸው ነበር። ያሉትም ጥምቀት ማለት ጌታችን በዮርዳኖስ እንደተጠመቀው በጥልቅ ነው እንጂ በመርጨት አጥምቁ የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ስለሌለ እኛ በዚህ መንገድ አንጠመቅም ብለው ሞግደው ነበር።

አለቃ ዘካሪያስም በነገሩ ስለተቸገሩበት ለተማሮቻቸው እንደሚከተለው አድርገው በትንቢት መልክ ነገሯቸው። «እኔ እናንተን እንድመራና እንዳስተምር የፈቀደልኝ እስከዚህ ድረስ ነው። ለወደፊቱ ግን መልካቸው መልካችሁን ቋንቋቸው ቋንቋችሁን የማይመስሉ ሰዎች ይመጣሉ። ስለጥምቀትም ሆነ ስለሌሎቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉት ትምህርቶች በሙላት ያስተምሯችኋል። በጥልቅም ያጠምቋችኋል። ምልክታቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ ስታገኙአቸው አንዱን ቃል በሶስት ቋንቋ ሲናገሩት ትሰማላችሁ» ብለው ስላግባቧቸው በዚያው እለት አብረው በመርጨት ተጠመቁ።

አለቃ ዘካሪያስ ከሞቱ በኋላ ከተማሮቻቸው አንዱ አለቃ ሞትባይኖር «በአስመራ ከተማ ወንጌልን በሙላት የሚያስተምሩ ሚሲዮናዊያን አሉ» የሚባል ወሬ ስለሰሙ ከቤጌምድር ተነስተው አንድ ወር ሙሉ በእግራቸው ተጉዘው አስመራ ከተማ ሲገቡ የስዊዲሽ ሚሲዮኖች በመልካም አቀባበል ተቀበሉአቸው።

አለቃም ከሚሽኖቹ ጋር ጥቂት እንዲቆዩ አንድ ቀን ቄስ ገብረሥላሴ የተባሉ ሰው አንድን ሕጻን «አሁን አጠምቅሃለሁ በኋላ አስተምርሃለሁ» በማለት በሳህን ውሃ ቀባ ቀባ አድርገው ሲያጠምቁት ያያሉ። ያን ጊዜ በአእምሮአቸው ነገሩ በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ ስርአት መሆኑን ስለተገነዘቡ አባታችን የተናገሩት ስለነዚህ ሊሆን አይችልም አሉ። የሚያጠምቁት በሕጻንነት ያውም በመርጨት የሚያከብሩት ቀዳሚትን ሳይሆን እሁድን ስለሆነ ሌሎች ካሉ ሌሎችን መፈለግ አለብኝ ይላሉ።

በቀጥሎው ሳምንት አንድ የማያውቁት ሰው መጥቶ ይዞአቸው በግጅረት ወደምትገኘው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ። በዚያችው እለት ሶስት ሰዎች በመድረኩ ላይ ቆመው ሲሰብኩ ይመለከታሉ። ሰባኪው አንድ አሜሪካዊ ሚሽነሪ ሲሆን የሚሰብከው በእንግሊዘኛ ነበር። ሶስተኛው የአገር ተወላጅ የሆኑት፣ ወደ ትግርኛ የሚተረጉሙት መምህር እቁባግዚ፣እንግሊዘኛ ስለማይችሉ ወደ ሚችሉት ወደ ኖርዌ ቋንቋ የሚተረጉም አንድ የወንጌል መልእክተኛ ነበር። እረሱ ወደ ኖርዌ ሲተረጉም መምህር እቁባግዚ የኖርዌ ቋንቋ በደንብ ይችሉ ስለነበር ከኖርዌጅን ወደ ትግርኛ ይተረጉሙ ነበር።

በዚህ ጊዜ ነው አለቃ ሞትባይኖር የትንቢቱን ፍጻሜ በአይናቸው ለማየት የበቁት። መልካቸው የርሳቸውን መልክ የማይመስል፣ቋንቋቸው የርሳቸውን ቋንቋ የማይመስል አንዱን ቃል በሶስት ቋንቋ ሲናገሩት ሰሙ። ከዚያም በመቀጠል ከስብከቱ በኋላ ከመሪዎቹ ጋር በመገናኘት ስለሰንበት፣ስለጥምቀት፣ስለ ባእድ አምልኮ እና ስለሌሎችም ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሠረተ የሚያረካ መልስ ስላገኙ ለሚሲዮኑ መሪዎች እንዲህ አሉዋቸው፥ «ትምህርታችሁን እኔ እና ወገኖቼ አስቀድመን በመጽሐፍ ቅዱስ ተረድተነዋል። አሁን መምህራን ብትልኩ እኔና ወገኖቼ እንቀበላችኋለን። ስለዚህ ሰው ላኩልን» ብለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ሚሲዮኑም ሰው ልኮ አለቃ ሞትባይኖር በሚኖሩበት መንደር የነበሩትን ወደ 200 የሚሆኑ አማኞች አጥምቀው በዚያች መንደር አንዲት ትምህርት ቤት ስላቋቋሙ በዚህ አይነት የአድቬንቲስት መልእክት በሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ሊጀመር ችሎአል። ታሪኩ ከሞላ ጎደል ይህን ይመስላል።

ለዚህ አጠር ላለ የእርማት መልእክት ፓስተር ጥሩነህን በአንባቢዎቻችን ስም ሆነን ልናመሰግን እንወዳለን። ደግሞ የቤተክርስቲያናችንን ታሪክ ሰፋ ባለ መልኩ በመጽሐፍ ደረጃ ጽፈው ለመጪው ትውልድ እንደሚያስቀሩም ተስፋ እናደርጋለን። ■

*አዘጋጆች*

***«ከሰማይ የወደቀው መልአክ** (ከገጽ1 የዞረ)* የፈጣሪን የፍቅር ሕግ እንዲተላለፉ አሳታቸው። «ያለ እግዚአብሔር ለዘላለም ትኖራላችሁ» ብሎ የሐሰትን ቃል ገባላቸው (ዘፍ 3፥1-17)። አዳምና ሔዋን የአምላክን ሕግ ስለተላለፉ ወደቁ። ሰይጣንም እንግዲህ «አለም በእጄ ውስጥ ገባች» ብሎ ማወጁን ጀመረ። «ዲያብሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው። የአለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፥ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው። ያን ጊዜ ኢየሱስ፥ ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው» (ማቴ፥48-10)

ሰይጣንና እርኩሳን መናፍስት የእግዚአብሔርን ሕግጋት ይጠላሉ። የእግዚአብሔርንም የፍቅር ሕግጋት የሚጠብቁትን ለማጥፋት ይመኛሉ፥ «ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፥በባህርም አሸዋ ላይ ቆመ» (ራእይ 12፥17)። ይህንን የተረዳው ሐዋሪያ ጴጥሮስ በ1ኛው መጽሐፉ ምእራፍ 5፥8 ላይ ሲመክረን፥ «በመጠን ኑሩ፣ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና» ይላል። ይህንን ታላቅ ምክር ክርስቲያኖች ችላ ማለት አይገባቸውም። በመጠን የሚኖሩና የነቁ ክርስቲያኖች በሰይጣን ፈተናዎች በቀላሉ አይታለሉም። ከክፋትና ከጥፋት ሁሉ በስተጀርባ በአይን የማይታይ አጥፊ የዲያብሎስ እጅ እንዳለ ያውቃሉ።

የሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ከ2000 አመታት በፊት ወደዚህች ምድር ሥጋ ለብሶ ሲመጣ አለም በጨለማ ተውጣ በሰይጣን ጨካኝ አገዛዝ ስር ወድቃ ነበር። ክርስቶስ ወደዚህች ምድር የምትባል የጦር ሜዳ ሲመጣም የሰይጣንን ሥራ አላማውንም ለማፍረስ ነበር። «ስለዚህም የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1ዮሐ3፥8)።

*(በገጽ 4 ይቀጥላል)*



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

## ጤናችን

# የጎመን የፈውስ ኃይል

ጥቅል ጎመን፣አበባ ጎመን ወዘተ በመሳሰሉት የተለያዩ የጎመን አይነቶች ውስጥ ያለው የፈውስ ኃይል ከዚህ በታች በአጭሩ ይገለጻል።

ጎመን ባክቴሪያዎችንና ቫይረሶችን ማጥፋት ከመቻሉ ሌላ የአካልን በሽታ የመከላከያ ኃይል (Immune System) ያጠነክራል። በጎመን ውስጥ ብዙ ቫይታሚን ሲ (Vitamin C), ብረት (Fe), ፖታሲያምና ካልሲየም (Ca) አለ። ጎመን በተለይ የሚታወቀው ካንሰርን በመግታት (በመዋጋት) ባለው ኃይል ነው። ለምሳሌ በሳምንት አንድ ጊዜ እንኳን ጎመን መመገብ የአንድን ግለሰብ በትልቁ አንጀት ካንሰር የመያዝን እድል በ60% ሊቀንስ ይችላል። አንድ በ1986 ዓ.ም. በጃፓን አገር የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው በምግባቸው ብዙ ጎመን የሚጠቀሙ ሰዎች በተለያዩ የካንሰር አይነቶች ተይዘው የመሞ ታቸው እድል ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል።



ጎመን ካንሰርን የሚዋጉ (Phyto Chemicals) በውስጡ አሉት። በጨጓራ ቁስል (Ulcer) ለሚሰቃዩ ሰዎች የጎመን ጭማቂ ታላቅ እርዳታና ፈውስ እንደሚሰጥ የተጠና ጉዳይ ነው። ዶ/ር ጋርኔት ቼኒ (ከስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ) ባደረጉት ጥናት መሠረት የጎመን ጭማቂ የጨጓራን ቁስል ማዳን ብቻ ሳይሆን በጨጓራ ቁስል ከመያዝም ሊከላከል እንደሚችል አሳይተዋል። በተጨማሪም በጎመን ውስጥ ያለው «ፋይበር» (fiber) በደም ውስጥ ያለውን የቅባት እና የስኳር መጠን የማስተካከል ችሎታ እንዳለው ይታወቃል። እንዲሁም ይህ «ፋይበር» የሆድ ድርቀትን መከላከል ይችላል።

የጎመን ጭማቂ ለተለያዩ አይነት የሆድ በሽታዎች፣ለጨጓራና የአንጀት ቁስል፣ቃር ለሚመሳሰሉት ታላቅ ፈውስ ነው። እንግዲህ ፈጣሪ በተፈጥሮ ውስጥ ያስቀመጠውን የፈውስ ኃይል እንዲጠቀሙበት እናበረታታዎታለን።■

*አዘጋጆች*

### ንስሃ ምን ያካትታል?

ንስሃ የፈቃድ ውሳኔ ነው
(ሉቃ 15፣17-18, ሐዋ 2፣38)

ንስሃ የእምነት ድርጊት ነው
(ሮሜ 7፥18 ሐዋ3፥19,26 ዮሐ 10፥27)

ንስሃ የአእምሮ መለወጥ ነው
(ሮሜ 3፣5-8 , ኤፌ 4)

ንስሃ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
(ሐዋ 5፣31, ዮሐ 16፣8, ሮሜ 2፣5 ዮሐ 6፣37)

ንስሃ በተከታታይ የሚያስፈልገን ነው
(1ዮሐ1፣5-6,9)

ንስሃ የእግዚአብሔር መጠይቅ ነው
(ሐዋ 17፣30, ሉቃ 13፣3-5)

ተፈጥሮአዊው ሰው በኃጢያቱ ከእግዚአብሔር ባይለይ ኖሮ ንስሃ አያስፈልግም ነበር።

*ምንጭ፥ አክትስ ማጋዚን*
*ትርጉም፥ ቶማስ ኃይሉ ከወልቂጤ*

---

*«ከሰማይ የወደቀው መልአክ* (ከገጽ3 የዞረ)

የእግዚአብሔር ልጅ አሰቃቂውን የመስቀል ሞት ከቀመሰበት ጊዜ ጀምሮ ዲያብሎስ ለዘላለም የተሸነፈ ጠላት ሆነ። ቢሆንም ግን ሰይጣን መሸነፉን በፈቃዱ ተቀብሎ እጁን አጣምሮ አልተቀመጠም። ከሰማይ እሳት ወርዶ ለዘላለም እስከሚያጠፋው ድረስ የማጥፋት ተግባሩንና ውጊያውን ይቀጥላል።

ብዙ ፀረ ሃይማኖት የሆኑ ሰዎች ሰይጣናት ሰዎች በአእምሮአቸው ውስጥ የፈጠሩአቸው ናቸው እንጂ በእውነት ያሉ ፍጡራን እንደሆኑ አያምኑም። በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት እነዚህ እርኩሳን መናፍስት ይህ ነው የማይባል ኃይል አላቸው። መልካሙ ዜና ግን እግዚአብሔር ከእነርሱ እጅግ ብርቱ መሆኑ ነው። ስለዚህም በአምላክ የሚታመኑ በፍቅር እቅፉ ውስጥ ያርፋሉ፣ሰይጣንም ሊያሸንፋቸው አይችልም። «እኔም የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ። ለዘላለምም አይጠፉም። ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፣ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ 10፥28-29) ብሎ የሱስ ይናገራል።

ስለዚህ ከሰማይ ስለወደቀው ስለተሸነፈው ጠላት ብዙ አናወራም። የእኛ ልብ የሚያስበውና የሚናፍቀው ጌታን ነው። ወደ ጌታ የበለጠ እየቀረብን ስንመጣ የሰይጣንን ተንኮልና ክፋት የበለጠ እንረዳለን። ግን ከሁሉ ይልቅ የአዳኙን ፀባይ ውበት ከነሙላቱ እናየዋለን። በዙሪያችን እንደሚያገሳ አንበሳ የሚዞረው ጠላት ምኞቱ የጌታን የፍቅር እጅ የምትለቅቀውን ነፍስ ሊውጣት ስለሆነ ከመድኃኒታችን አንለይም።

ሉሲፈር ከመጀመሪያው ገና በትእቢት ኃጢያት እንደሠራ እግዚአብሔር ቢያጠፋው ኑሮ በመልእክታችን መጀመሪያ ላይ የጠቀስናቸው ስቃዮችና ችግሮች ሁሉ ባልመጡ ነበር» የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። በርግጥ አምላክ ሰይጣንንና እርኩሳን መናፍስትን ከመጀመሪያው ሊያጠፋቸው ይችል ነበር። ነገር ግን ይህንን አላደረገም። ለምን? እግዚአብሔር ፍቅር እንጂ አምባገነን ስላልሆነ። አምላክ ከመጀመሪያ ለፍጥረቱ የመምረጥ ችሎታና እድል ሰጥቶታል። አምላክ የፈጠረውን ሕያው ፍጡር እንደ ቁሳቁስ እቃ አይመለከተውም። ፍጡር በፈጣሪው ላይ ሲያምጽ የፍቅር አምላክ ልቡ በሐዘን ይሰበራል፣የጠፋውንም ለማዳን ይሞክራል እንጂ ወዲያውኑ ከመኖር ወዳለመኖር አይለውጠውም። እግዚአብሔር የሚወደው እና ውብ አድርጎ የፈጠረው መልአኩ ሉሲፈር ተጸጽቶ በመንግሥቱ አገልግሎቱን እንዲቀጥል ምኞቱ ስለነበር ሁሉንም ሞከረ። ግን የሉሲፈር ልብ ጭራሹን አመፀ።



አምላክ ያመፁትን መላእክት በሙሉ ከመቅጽበት ቢያጠፋቸው ኖሮ ሉሲፈር ቀድሞ ስለፈጣሪው ያስፋፋው የሐሰት ወሬ አብሮ ይጠፋል ማለት አይደለም። እንዲያውም ይህ ድርጊት ወሬውን ያባብስ ነበር። ሌሎችም ኃጢያትን የማያውቁ ታዛቢ ፍጡራን እግዚአብሔርን እንደ ጨካኝ ገዳይ ይቆጥሩ ነበር። በተጨማሪም ሌሎቹ በእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የጸኑት መላእክት አምልኮአቸው ከፍቅር የተነሳ ሳይሆን ከፍርሃቻ የተነሳ ይሆን ነበር። ከፍርሃቻ የተነሳ መገዛትም ከጊዜ በኋላ ለሌላ አመጽ መንገድ መክፈቱ አይቀርም። ስለዚህ ሁሉን የሚችለው ኤልሻዳይ የሆነው አምላክ ሌላ መንገድ መረጠ። ይኸውም ከሰማይ የተጣለው መልአክ ከነአጃቢዎቹ እውነተኛ ጸባዩንና አላማውን ለአለማት ሁሉ እንዲያሳይ ጊዜና እድል ሰጠው። በዚህ መንገድ በፈጣሪ ላይ ማመጽና የፈጣሪን የፍቅር ሕግጋት መጣስ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ለሁሉም መታየት ግድ ነበረበት። ከሁሉ በላይ ግን የእግዚአብሔር እውነተኛ የፍቅርና የርህራሄ ባህርይ እንዲሁም እውነትና ጽድቅ በዚህ ዛሬም ቢሆን የእኛን ሕይወት በሚመለከተው በብርሃንና በጨለማ መካከል በሚደረገው ታላቅ ተጋድሎ መገለጽ ነበረበት።

በመጨረሻም ግን እግዚአብሔር የወሰደው እርምጃ ትክክለኛ መሆኑ ለፍጥረታት ሁሉ ይታያል፥ «ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፥የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ጌታ ሆይ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ ...» (ራእይ 15፥3-4)■

*ዳዊት መንግሥቱ*


Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት - ክፍል 3

**ተከታታይ ትምህርት**



## ሰርዴስ
(ራእይ 3፥1-6)

በትያጥሮን ወዳለው ቤ/ክ የተላከው መልእክት «በጨለማው ዘመን» ለነበረው የጳጳስ ስርአት ነበር። ይህ የሰርዴስ መልእክት ደግሞ ራሷን ከዋናው ቤ/ክ (Mother Church) ለተገነጠለችው የፕሮቴስታንት ቤ/ክ የተላከ ነበር። እነዚህ የተገነጠሉት አማኞች የኤልዛቤልን የሀሰት ትምህርት አንቀበልም ያሉ ለወንጌል ታማኝ ሁነው የቆሙ ሰዎች ነበሩ።

በዚያን ወቅት በቤ/ክ ላይ ሰፍኖ የነበረውን የሀሰት ትምህርት በመቃወም ከተነሱት የመጀመሪያ ሰዎች ውስጥ አንዱ ጆን ዊክሊፍ ነበር። ይህ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ በመተርጎም «የተሐድሶ (Reformation) የንጋት ኮከብ» በመባል ይታወቃል። ዊክሊፍ የሚጽፋቸው ጽሑፎችም ዝናን እያተረፉ መጡ። መጽሐፍ ቅዱስን ማንኛውም ተራ ሰው አንብቦ ሊረዳ እንደሚችልም ብዙ ሰዎች እየተገነዘቡ መጡ።

ሌላ ጆን ሀስ የተባለ ሰው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ቀላል በሆነ ቋንቋ በድፍረት መስበክ ጀመረ። በዚያን ወቅት ይህንን አይነት ድርጊት በጳጳሱ ስርአት ስር ባለችው ቤ/ክ የተከለከለ ነበር። ጆን ሀስ ዊክሊፍ የጻፋቸውን ጽሑፎች በመሰብሰብ በደንብ ያነባቸው ጀመር። ቀስ በቀስም ልቡ ከሮም ቤ/ክ እየራቀ መጣ። ቤ/ክ በምእመናን ላይ የምታደርገውን ጭቆና በመቃወም ነፍሳት በክርስቶስ ላይ ብቻ ሙሉ እምነት እንዲኖራቸው ያደፋፍራቸው ጀመር። ከእንግደዚህ አይነት የማይነወጥ እምነቱ የተነሳ የሮም ቤ/ክ በእሳት ተቃጥሎ እንዲገደል አደረገችው።

የተሐድሶ እሳት ግን መቀጣጠሉን ቀጠለ። ከጀርመን አገርም ኃያልና ግልጽ የሆነው የማርቲን ሉተር ድምፅ ተሰማ። ማርቲን ሉተር ትሁት የካቶሊክ መነኩሴ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት እሳት በልቡ ከመቀጣጠሉ የተነሳ ቤተክርስቲያኑ ከምታስተምረው በሙላት የሚቃረን ትምህርት ይዞ ተነሳ። በምእመናን ፊት መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ከፍ አድርጎ በማንሳት ከጳጳሶችና ከነገሥታት ቃል ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚበልጥ ማወጅ ጀመረ። በዚህ መንገድ በብዙ የሚቆጠሩትን በሀሰት የተጠመዱትን ነፍሳት በመወከል በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ቆመ። ደህንነት አንድ ሰው በሚሠራው መልካም ተግባር ሳይሆን የጸጋ ስጦታ እንደሆነ ለማሳየት ቻለ። ምንም እንኳን በዙሪያው ተቃውሞ ቢያስቃየውም እርሱ ግን በእውነት ጸና።

በፈረንሳይ አገር ደግሞ ጆን ካልቪን የተባለ አንድ ወጣት ተነሳ። በሥራ ለመጽደቅ መሞከር ሀሰት እንደሆነ ለነፍሳት እያስተማረ ሰዎች ለደህንነታቸው ክርስቶስን ብቻ ማመን እንደሚገባቸው ያስገነዝባቸው ጀመር። ካልቪን ፈረንሳይ ወደ ፕሮቴስታንት እምነት እንድትዞር ታላቅ ሙከራ አደረገ። ይህም የካቶሊክን ቤ/ክ አበሳጨ። ታላቅ ስደትም ደረሰበት።

እንደዚህም በተለያዩ ቦታዎች (ዊልያም ታይንዴል በእንግሊዝ፣ሜኖ ሳይመንስ በሆላንድ፣ ታውሰን በዴንማርክ በኋላም ዌስሊ በእንግሊዝ...) የተለያዩ ሰዎች የወንጌል እውነት የጥንት ቦታውን ዳግም እንዲይዝ ታላቅ አስተዋጽኦ አደረጉ። የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትም እየተመሠረቱ መጡ። የጳጳስ ስርአት እየተዳከመ መጣ። ነፍሳት የራሳቸውን ውሳኔ እንዲወስኑ ነጻ ወጡ።

ምንም እንኳን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ለተሐድሶ መነሳት ታላቅ አስተዋጽኦ ቢያበረክቱም በተወሰኑ እምነቶች ላይ ብቻ በማተኮር ሌላ ተጨማሪ ብርሀን ከእግዚአብሔር ቃል እንዳይቀበሉ አእምሮአቸውን ዘጉ። ከሮም ስልጣን በመላቀቃቸው ኩራት እየተሰማቸው አስቀድሞ ሲወቅሱት የነበረው የሮም የመከፋፈልና የአለመቻቻል መንፈስ ቀስ በቀስ በእነርሱም ውስጥ ስር እየሰደደ መጣ። ከአስመሳይነትና ከሞተ ሥራ ለመላቀቅ ብለው የጀመሩትን ተሐድሶ እስከመጨረሻው ከማድረስ ይልቅ የአስመሳይነት መንፈስ እንደ ጥቁር ደመና በላያቸው ያንዣብብ ጀመረ።

### ሕያው እንደመሆንህ ሞተህማል

ቤ/ክ ከላይ የተጠቀሰው አይነት ሁኔታ ላይ ባለችበት ጊዜ ነበር ይህ የሰርዴስ መልእክት የተላከው። የሱስ በዚህ መልእክት የክርስቲያኖችን ሁኔታ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ ይገልጻል። «ሕያው እንደመሆንህ ስም አለህ ሞተህማል»። የፕሮቴስታንት (የተሃድሶ) ቤ/ክ ራሷን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ባደረገችው ሙከራና ለወንጌል ስላላት ጥረት ትታወቅ ነበር። እንደዚህም ሁኖ ግን በክርስቶስ አነጋገር ሙታ ነበር። የተሐድሶ ጀማሪዎች ግን በእውነት ሕያዋን ነበሩ። ከጊዜ በኋላ ግን ቤ/ክ የእውነትን አርማ ወደፊት ከማስተላለፍ ይልቅ የፕሮቴስታንቶች እምነት ልክ እንደ ጳጳሱ ስርአት አስመሳይ እየሆነ መጣ።

በዊክሊፍ በሉተርና በሌሎቹ የተጀመረው ተሐድሶ «በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ ወይም ፍጹም አልነበረም» (ራእይ 3፥2) አብያተ ክርስቲያናትም ይህ የጎደለው እውነት እንዲሞላ ፈቃዳቸውን አላሳዩም። አዲስ የተቀበሉአቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ችላ እያሉ መምጣት ብቻ ሳይሆን ዋና ዋና ምሰሶዎቻቸውንም መጠራጠርና መልቀቅ ጀመሩ (ለምሳሌ፥ የድንግልን መውለድ፣የክርስቶስ ሥጋ ለብሶ መምጣት፣መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን)።

### እንደሌባ እመጣብሃለሁ

እንግዲህ የሰርዴስ ቤ/ክ በመንፈሳዊ ሞት ውስጥ ስለነበረች የሱስ «እንደሌባ እመጣብሃለሁ» እያለ ያስጠነቅቃታል። ይህ «እንደሌባ እመጣብሃለሁ» የሚለው ክፍል እዚህ ላይ የሚያመለክተው ስለ የሱስ ዳግም ምጽአት ሳይሆን የሱስ ወደ እያንዳንዱ ነፍስ ለፍርድ እንደሚመጣ ለማሳየት ነው። ክርስቶስ በታላቅ ክብር ዳግም ከመምጣቱ በፊት ልብሳቸውን በበጉ ደም ያነጹትን ወይንም ልብሳቸውን ያቆሸሹትን ለመለየት አስቀድሞ ፍርድን ያከናውናል (ሚክ 3፥1,2,5)

### የድል ነሺው ሽልማት

ስህተትን በማይሠራው፣ውሳኔው ዘላለማዊ በሆነው አምላክ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ መጻፍ እንዲሁም የአንድ ግለሰብ ስም በእግዚአብሔር ፊት መጠራቱ በጣም ክቡር ነገር ነው። «ድል የነሳው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጎናጸፋል፣ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፣በአባቴና በመላእክቱ ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ» (ራእይ 3፥5)።■

### ዘመኑን እንዋጅ

የእግዚአብሔር ቁጣ ያለምህረት አይደለም። የምህረት እጁ አሁንም እንደተዘረጋ ነው። መልእክቱ በመላው ኒው ዮርክ (New York) መተላለፍ አለበት። ሰዎች እስከ ፍርድ ቀን ያከማቹትን ንብረት እግዚአብሔር በቀላሉ ሊያጠፋ እንደሚችል መገንዘብ አለባቸው። (Manuscript Releases, Band 3, p. 310-311, 1902)

የኒው ዮርክን እጣ በተመለከተ የተለየ ብርሃን አልተሰጠኝም። የማውቀው ነገር ቢኖር፤ታላላቆቹ ሕንጻዎች አንድ ቀን እንደሚፈራርሱ ነው።... ሁሉም ቦታ ሙታን ይኖራሉ። ስለዚህም ነው ከልቤ በከተሞቻችን የሚኖሩ ሰዎች ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው የምሻው። (Review & Herald, 5.7.1906)

አንድ ቀን ኒው ዮርክ ውስጥ እያለሁ በሌሊት (በህልም) ታላላቅ የሆኑ ሕንጻዎች ሲገነቡ ታየኝ። ለሕንጻዎቹ ባለቤቶችና ለገነቧቸው መሃንዲሶች ክብር የተገነቡት እነዚህ ሕንጻዎች የተሠሩት በእሳት መቃጠል እንዳይችሉ ተደርጎ ነበር። ከዚያ ወዲያው በመቀጠል እሳት አደጋ ሲጠራ አየሁ። ሰዎች ሊቃጠሉ አይችሉም እያሉ ሲናገሩላቸው የነበሩት እነዚህ ሕንጻዎች በፍጥነት እሳት ሲበላቸው አየ። የእሳት አደጋ ሠራተኞች እሳቱን ሊገቱ አልተቻላቸውም፣እሳት ማጥፊያ ጎማቸውንም ሊጠቀሙ አልቻሉም። (Testimonies for the Church, Band 9, p.11-13, 1909)





Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com



## የትንቢት መንፈስ

# የተስፋፋው ተቃርኖ (ክፍል 2)

ውድ የትንቢት ቃል አንባቢያን፥ ካለፈው እትም ጀምሮ«The Great Controversy» ወይም «ታላቁ ተጋድሎ» ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሰባት ምእራፎች በተከታታይ በማቅረብ ላይ ነን። ይህ መጽሐፍ በ19 መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20 መቶ ክ.ዘ. መጀመሪያ ላይ በ ኤለን ጂ ኋይት የተጻፈ ሲሆን ወቅታዊ እውነትን የያዘ በመሆኑ ለአንባቢያን በረከት ይሆናል ብለን እናስባለን።

«ሰዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመታዘዝ ነጻ ወጥተዋል» የሚለው ትምህርት የግብረ ገብነትን ግዴታ አድክሞአል። በአለም ላይም አመጻ እንዲበዛ በርን ከፍቶአል። ስርአተ አልባነት፣ብኩንነትና የአመጽ ሥራ እንደሚያስፈራ የማእበል ጎርፍ አጥለቅልቀውናል። በቤተሰብ ውስጥም ሰይጣን በሥራ ላይ ነው። «ክርስቲያን ነን» በሚሉ ቤቶችም እንኳን ሳይቀር ሰንደቅ አላማውን ያውለበልባል። በነዚህ አይነት ቤተሰብ ውስጥ ክፋት፣ምቀኝነት፣ህውከት፣ግብዝነት፣አለመጣጣም፣ፉክክር፣ጠብ፣መካካድ፣ስግብግብነትና ከመጠን ያለፈ ምኞት ይታያል።

ወንጀል በመሥራታቸው ምክንያት በእስር ቤት የሚገኙት ከባድ ወንጀለኞች አብዛኛውን ጊዜ ትልቅ ጀብዱ እንደሠራ ጀግና ስጦታና ምስጋና ሲሰጣቸው ይታያል። በሠሩት ወንጀልና ባሳዩት መጥፎ ፀባይ በሕዝብ ፊት ሞገስ እንዲያገኙ ይደረጋል። ጋዜጠኞች አንድ ወንጀለኛ የሠራውን ወንጀል በዝርዝሩ በመጻፍ ሌሎችም እንደዚሁ ያንን የማታለል፣የንጥቂያና የነፍስ ግድያ ሥራ እንዲሠሩ መንገድ ይከፍታሉ። ሰይጣን ይህ ሲኦላዊ መርሀ ግብሩ ስለተከናወነለት ይደሰታል። ወንጀልን የመሥራት ፍቅር፣ግድያን የመፈጸም የጋለ ፍላጎት፣ራስን ያለመግዛትና የአመጽ መብዛት የእግዚአብሔር ሰዎች «ይህንን የክፋት ማእበል ለመቋቋም ምን ማድረግ ይቻላል?» የሚለውን ጥያቄ እንዲጠይቁና እንዲመረምሩ ሊያነሳሳቸው ይገባል።

ፍርድ ቤቶች ተበላሽተዋል (ተበክለዋል)። መሪዎች በሥጋዊ ደስታና በማካበት ፍላጎት ተይዘዋል። ራስን ያለመግዛት የብዙዎችን አእምሮ አበላሸ፤ከዚህም የተነሳ ሰይጣን ሰዎችን ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠራቸው ትንሽ ቀርቶታል። የሕግ ባለሙያዎች ከትክክለኛው መንገድ ርቀዋል። ጉበኞችና የሚሸነግሉም ሆነዋል። ሰካራምነትና ጸብ፣ስሜታዊ ምኞትና ምቀኝነት እንዲሁም ሐቀ ቢስነትና ክፉ ሥራዎች ሕግን በሚያስፈጽሙ ግለሰቦች መካከል ይገኛሉ። ነቢዩ ኢሳያስ እንዲህ ብሎ ነበር፥- «ፍትህ ከእኛ ርቆአል፤ጽድቅም በሩቁ ቆሞአል፤እውነት በመንገድ ላይ ተሰናክሎአል፤ቅንነትም መግባት አልቻለም» (ኢሳ 59፥14)።

በታላቋ ሮም ቤ/ክ ጊዜ እያደገ የመጣው አመጻና መንፈሳዊ ጽልመት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መጨቆን አይቀሬ ውጤት ነው። ነገር ግን በሃይማኖት ነጻነት ዘመን፣የወንጌል ብርሃን እያበራ ባለበት ጊዜ፣ አለም አቀፋዊ የሆነ እምነተቢስነት፣የእግዚአብሔርን ሕግ አለመቀበልና በዚያም ምክንያት የመጣው ምግባረ ብልሹነት መንስኤ ምን ይሆን? ዛሬ ሰይጣን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያነቡ በመከልከል አለምን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ስለማይችል፤ያንኑ አላማውን ከግብ ለማድረስ ሌላ ብልሃት ይፈልጋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን እምነት ማጥፋት ራሱን መጽሐፍ ቅዱስን የማጥፋት ያህል ስለሆነ ይህንን ግቡን ለመምታት ይጥራል።



*«ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ በሚረግጡበት ወቅት የሕግ አውጭውን ስልጣን ይክዳሉ»*

«የእግዚአብሔር ሕግ በሰዎች ላይ አይጸናም» የሚለውን በማስተማር ሰዎች ትእዛዙን ፈጽሞ ሰምተው እንዳላወቁ ያህል እንዲተላለፉት ይመራቸዋል። በድሮ ጊዜ እንዳደረገው አሁንም አላማውን ለመፈጸም ቤተክርስቲያኒቱን መሳሪያ በማድረግ ይጠቀማል። የዘመኑ የሃይማኖት ድርጅቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽ ሆነው የተቀመጡትንና በብዙ ሰዎች ታዋቂነት የሌላቸውን እውነቶች ላለመቀበል ወሰኑ። በአንጻሩም የራሳቸውን ትርጉም በማበጀት የጥርጣሬ ዘር የሚዘራባቸውን አቋሞች ያዙ። «ሰው ሲሞት ነፍሱ ሕያው ነች» «ሰው ከሞተ በኋላ የሚያደርገውን ያውቃል» የሚለውን ጳጳሳዊ የሀሰት ትምህርት አጥብቆ በመያዝ እነርሱን ከ«ስፒሪቲዝም» (Spiritism) የማታለል ሥራ ሊጠብቃቸው (ሊከላከልላቸው) ይችል የነበረውን እውነት ካዱ (ጣሉ)። ስለ ዘለአለማዊ ስቃይ የሚሰበከው ትምህርት ብዙዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጠራጠሩ መርቷቸዋል (አድርጎአቸዋል)።

የአራተኛው ትእዛዝ ትርጉም ለሰዎች ግልጽ በሚደረግላቸው ጊዜ እና ሰዎች ሰባተኛውን ቀን ሰንበት (ቅዳሜን) የማክበር ግዴታ እንዳለባቸው ግልጽ በሚሆንበት ጊዜ ያኔ ብዙ ታዋቂና ዝነኛ መምህራን ትእዛዙን መጠበቅ ስለማይፈልጉ «የእግዚአብሔርን ሕግ የመጠበቅ ግዴታ የለብንም፣የእግዚአብሔር ሕግ ተሽሮአል፣መጠበቅም አያስፈልግም» በማለት ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ይሞክራሉ። በዚህም አኳኋን ሕግንና ሰንበትን አንድ ላይ ውድቅ ያደርጋሉ። ሰንበትን መልሶ የማቆም (የማደስ) እንቅስቃሴ እየተስፋፋ በሚመጣበት ጊዜ ይህንን አራተኛ ትእዛዝ የሚለውን ላለሟሟላት ብቻ ሲባል የመለኮታዊውን ሕግ ማጥላላትና መካድ የተለመደ ነገር ይሆናል።

ኃላፊነት ያላቸው የሃይማኖት መሪዎች የሚያስተምሩት ትምህርት ለእምነተ ቢስነት፣ለ ስፒሪቲዝም እና የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ ለመናቅ በር ከፍተዋል። በክርስቲያኑ አለም ለሚታየው አመጽ እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ከባድ ኃላፊነት አለባቸው። እንዲያውም እነዚህ መሪዎች «እንደዚህ በፍጥነት እየተስፋፋ ያለው ብልሹነት የመጣው የክርስቲያኖችን ሰንበት (እሁድን) በማርከስ ምክንያት ነው» ብለው ይናገራሉ። «እሁድን የመጠበቅ ግዴታም የሕብረተሰቡን የሞራል ሁኔታ በብዙ ያሻሽለዋል» በማለት ይመክራሉ። ይህ አባባል በተለይ የእውነተኛው የሰንበት እውነት ትምህርት በተሰበከባት በአሜሪካ አገር በይፋ ይነገራል። በዚሁ አገር ሥነ ምግባርን (ሞራል) ለማሻሻል ጠቃሚ መሳሪያ የሆነውን የመሻትን መግዛት (ቴምፔራንስ) ትምህርት ብዙ ጊዜ ከእሁድ እንቅስቃሴ ጋር በማዋሃድ ይቀርባል።

እነዚህ የእሁድን እንቅስቃሴ የሚያካሂዱት ሰዎች «የሕብረተሰቡን ከፍተኛ ፍላጎት ለሟሟላት እየሠራን ነን» ይላሉ። ከእነርሱ ጋር ለመተባበር ያልፈለጉቱ ደግሞ «የመሻትን መግዛትና የተሃድሶ ጠላቶች ናቸው» ተብለው ይወገዛሉ። ነገር ግን ሀሰትን ለማቋቋም (ለማስፋፋት) ሲባል መልካም ከሆነው አላማ ጋር አንድ የመደረጉ እውነት ሀሰቱን ለመደገፍ የሚረዳ ማስረጃ አይደለም። መርዝን ከደህና ምግብ ጋር በመደባለቅ ልንሸፍነውና ልንደብቀው እንችላለን፤የመርዝነት ባህርዩን ግን ልንቀይረው አንችልም። እንዲያውም ያላወቁት እንዳለ ሊመገቡት ስለሚችሉ

(በገጽ 8 ይቀጥላል)

### የሃያ ሚሊዮን ዶላሩ ሽርሽር (ከገጽ 1የዞረ)

ብዙ ጊዜዬን አሳልፍ የነበረው ስለ ኮከቦች፣ፕላኔቶች ባጠቃላይ በጠፈር ስላሉት ነገሮች ሁሉ በመመርመር ነበር። እንደ ማርክ የኔም ዋና ምኞት አንዴ ወደ ጠፈር ሄጄ በዛ የሚገኙትን ከዋክብት ማየትና መድነቅ ነበር። ስለዚህ ማርክ ሕልሙ ስለተሳካለት የተደሰተውን ደስታ ለመረዳት እችላለሁ።

የአለማትን ሁሉ ፈጣሪ፣የእኛን ፕላኔትና በጠፈር ውስጥ ያሉትን ተቆጥረው የማያልቁትን አለማት ሁሉ የሠራውን አምላክ የተዋወቅሁ ጊዜ ግን ለኃጥያቴ ሲል ስለሞተልኝ ከኃጥያት ባርነት ስላወጣኝ ብቻ ሳይሆን፤ያንን የልጅነት ጊዜዬን ሕልም አንዴ እንደሚፈጽምልኝ ሳውቅ እጅግ በጣም ሐሴት አደረግሁ። ማለትም ጌታ የሱስ ከሰማይ መላእክቱ ጋር ተመልሶ ሲመጣ ወደሰማይ ይዞኝ እንደሚሄድ በዚያም ከሱ ጋር ሆኜ ሌሎች በኃጥያት ያልወደቁትን አለማት እንደምጎበኝ ስረዳ ከመጠን በላይ ናፍቆቴ በረታ።

ዛሬ ይህንን የጠፈር ጉዞ በጉጉት በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ። ጉዞው በነጻ ነው። እንደ ማርክ ሃያ ሚሊዮን ዶላር መክፈል የለብኝም፤ቢሆንም ማርክ ይህንን ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት ለረጅም ጊዜ ዝግጅት ያደርግ እንደነበር እኔም ልዘጋጅ ይገባኛል። በቂ ዝግጅት እንዳደርግ ደግሞ እግዚአብሔር መመሪያውን መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶኛል።

ማርክ ምናልባት አንድ ተራ ሰው ያላየውን በሕዋ ውስጥ ያሉትን ብዙ ነገሮች አይቶ ይሆናል፣ግን አንድ ጊዜ የሱስ በሱ የሚያምኑትንና የሚታዘዙትን ወደሰማይ ይዞ ሲሄድ «አይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው» ተብሎ በ 1ቆሮ2፥9 እንደተጻፈ፤የዚያን ጊዜ ለማመን እስኪያቅተን ድረስ ሕልማችን እውን ሆኖ እናገኘዋለን።

ምናልባት ማርክ የደህንነትን ምስጢር ቢረዳ ኖሮ ይህንን ገንዘቡን በመልካም ነገር ላይ በማዋል ስሙን ያስጠራ ነበር። ይህን በማድረጉ ምናልባት «የጠፈሩ ጀግና» በመባል ፈንታ «ቸሩ ጀግና» የሚል ቅጽል ስም ይሰጠው ነበር። ውድ አንባቢ ሆይ፥ አንድ ጊዜ ድል ነስተን በሰማይ በምንገኝበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእርስዎና ለእኔ የሚሰጠን አዲስ ስም አለ፤ ያ ምን ይሆን?■

ዳዊት መሐሪ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# ምስክርነት



## «የበረሃ ሕይወቴ ለመለመች»

የተወለድኩት አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን እስከ 12 አመት እድሜዬ ድረስ ያደግሁት በዚያችው ዋና ከተማችን ውስጥ ነበር። አባቴ በወታደርነት ሲያገለግል ሳለ ሞተ። ከሱ ሞት በኋላ የትምህርት እድል ደርሶኝ ወደ ኩባ አገር ሄድኩኝ። በዚያም ለ15 አመታት ያህል ቆይቼ ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ አሁን ወዳለሁበት ወደ ስፔይን አገር መጣሁ። እነሆ በዚህ አገር መኖር ከጀመርኩ ስምንት አመት ሆነኝ።

የተወለድኩትና ያደግኩት በኦርቶዶክስ ቤተሰብ ውስጥ ነው። ከድሮም ጀምሮ ስለመንፈሳዊ ነገሮችና ስለሃይማኖት ጥሩ ፍላጎት ነበረኝ። ኩባ አገርም ከገባሁ በኋላ በሕጻንነቴ የተማርኩትን ሁልጊዜ አስታውስ ነበር። ቢሆንም ከጌታዬ ጋር ጠንካራ የሆነ የግል ግንኙነት የጀመርኩት እንደገና ዳግም ከተወለድኩ በኋላ ነው። ማለቴ የሱስ ክርስቶስን የሕይወቴ መሪ እንዲሆን ከወሰንኩ በኋላ ነው። ጌታ የሱስን ያወቅሁት ኩባን ለቅቄ ለመውጣት 6 ወራት ሲቀሩኝ ነበር። በዚያን ወቅት ከባድ ችግር ውስጥ እገኝ ነበር። ምንም እንኳን ጌታ የሱስ እ.አ.አ. በ1987 ዓ.ም. ላይ የመጀመሪያውን ጥሪ ቢያደርግልኝም ጥሪውን የተቀበልኩት ሰኔ 25 1994 ዓ.ም. ነበር። ይህም ጥሪ የደረሰኝ በአንድ አድቬንቲስት ኩባዊ ጓደኛዬ አማካኝነት ነበር።

ወደ እስፔን አገር የደረስኩት ጌታ የሱስን እንደግል አዳኜ አድርጌ በተቀበልኩት በሳምንቴ ነበር። ስፔይን የአውሮፓ ክፍለ አለም አካል እንደመሆንዋ መጠን እንደሌሎቹ የሰለጠኑ የአውሮፓ አገሮች ለመንፈሳዊ ነገሮች ፍላጎት ጭራሽ የማይታይባት አገር ነች። በአብዛኛው ባሕላዊ ነገሮችና ልምዶች ይበዛሉ። ቢሆንም መንፈሳዊ ሕይወቴ እያደገና እየበለጸገ የመጣው በዚህ አገር ውስጥ ነው። እነሆ ዛሬ ከእግዚአብሔር እርዳታ ጋር በሕይወት ሸለቆና ተራራ ወደፊት እየተጓዝኩኝ ነው። ያቺ በበረሃ እንደተተከለ ወይን የነበረችው የቀድሞ ሕይወቴ እነሆ ለምልማ ፍሬዎች ማሳየት በመጀመሯ በጣም ተደስቻለሁ።

ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በሰጠኝ የተለያዩ ስጦታዎች አማካኝነት ጌታን በማድሪድ ከተማ በሚገኘው አንድ አድቬንቲስት ቤ/ክ ውስጥ በማገልገል ላይ እገኛለሁ። በተለይ ስፓኒሽ በሚናገሩ ሰዎች መካከል ማገልገል ያስደስተኛል። ከሁሉ ይልቅ በጣም የሚያስደስተኝ ስለጌታ መመስከር ነው። እግዚአብሔር አጋጣሚዎችን ሲያመቻችልኝ ለማገኛቸው ሰዎች ሁሉ እሱ ስላደረገልኝ ምህረትና ቸርነት እነግራለሁ፣መጽሐፍ ቅዱስንም አስተምራለሁ፣መንፈሳዊ ጽሑፎችንም አድላለሁ። ጌታ የሱስ ለሁለት ነፍሳቶች መዳን ምክንያት ስላደረገኝ እጅግ ከልቤ አመሰግነዋለሁ። አንዳንድ ጊዜ የአሁኑን ሕይወቴን ከቀድሞው ጋር ሳነጻጽረው ትልቅ ልዩነት እንዳለው አያለሁ። ጌታን ከማወቁ በፊት እኖር የነበረው ኑሮ ትርጉም የሌለው ነበር። ክርስቶስ ወደ ሕይወቴ ከገባ በኋላ ግን እለት በእለት ሲመራኝ ይሰማኛል። በእርሱ እርዳታ ከድል ወደ ድል እየተራመድኩ ነው። በርግጥ ብዙ ችግሮች ያጋጥሙኛል ነገር ግን የነገሥታት ንጉሥ እና የኃያላን ሁሉ ኃያል አምላክ ከኔ ጋር ስለሆነ የምታገለው የሕይወት ትግል ከተሸነፈ ሠራዊት ጋር መሆኑን ስለማውቅ ደስ ይለኛል። ዛሬ ሕይወቴ በእግዚአብሔር ቸርነት እንደዚህ ከሆነች ነገ ደግሞ እጅግ በጣም የላቀች እንደምትሆን ጌታ የሱስ ቃል ገብቶልኛልና አልፈራም።

እግዚአብሔር ከፈቀደ ወደፊት በሜዲካል ሚሽነሪነት ማገልገል እፈልጋለሁ። ይህንን እንዳቅድ ያነሳሳኝ ምክንያት፥ ያለ ተስፋ የሚኖሩትን ሰዎች በማገልገል እነርሱ ከፈጣሪያቸው ጋር እንዲተዋወቁና እንዲያገለግሉት ከዚያም ባሻገር ከየሱስ ክርስቶስ ጋር ለዘላለም እንዲኖሩ ማዘጋጀት ስለምፈልግ ነው። በተጨማሪም በበሽታ ለሚሰቃዩት ሰዎች ተስፋ እንዳላቸው የምሥራች ለመንገር በማሰብ ነው። ጌታ ከፈቀደ ደግሞ ቤተሰብ የመመስረት ሃሳብ አለኝ። በተለይ በአሁኑ ዘመን ሰይጣን ቤተሰብን በሚያጠቃበት ጊዜ እንደዚህ አይነት ሃሳብ ማሰብ ቀላል አይደለም። ቢሆንም እግዚአብሔርን በጸሎት በመጠየቅና ፈቃዱን የሚያሟላ ውሳኔ ለማድረግ እፈልጋለሁ። በርግጥ ይህ በለዘብተኝነት ወይም በቸልተኝነት የሚታይ ነገር አይደለም። ለትዳር ሊሆን ይችላል ብለን የምናቅደው ሰው የእምነታችን ተካፋይ መሆን እንዳለበት መዘንጋት ትልቅ ስህተት ነው። ምክንያቱም የቀን ልጆች ከጨለማ ልጆች ጋር ምንም አንድነት የላቸውምና።

በመጨረሻ ለዚህች መጽሔት አንባቢያን መናገር የምፈልገው ነገር አለ፥ ውድ አንባቢያን ሆይ! አሁን በእጃችሁ ውስጥ ያለችው ለታላቁ የበጉ ሠርግ እንድንቀርብ የምታደርገን መለኮታዊ መልእክት ያዘለች መጽሔት ስትሆን፣ይህንን የሠርግ ጥሪ ለወገኖቻችን ለጓደኞቻችንና ላገኘነው ሰው ሁሉ ግብዣው በነጻ መሆኑን እንንገር። ውድ አምላካችን እግዚአብሔር የሰጠንን መለኮታዊ ሥራ ከእርሱ ጋር ተባብረን በመሥራት የጠፉ ወገኖቻችንን ለማዳን መጣር አለብን። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወትን በየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በነጻ እንደሰጠን በማመንም ገና ካሁኑ ሐሴት እናድርግ። ጌታ ይባርካችሁ!

*ሐይሉ ኪ/ማሪያም ረዳ, ከስፔይን*

ውድ አንባቢያን!

ይህች የምስክርነት አምድ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዴት አድርጎ ከድቅድቅ የኃጢያት ጨለማ አውጥቶ ወደ ሚደነቅ ብርሃን እንዳመጣቸውና ትእዛዙን ከሚጠብቁት እንዲሁም የሱስን በማመን ከሚጸኑት ሕዝቡ ጋር እንደቀላቀላቸው የምናሳይበት አምድ ነው። የእርስዎንም ታሪክ ጌታ የሱስ እንዴት እንደቀየረውና የሰማይ ቤት ወራሽ እንዲሆኑ እንዳደረገዎ ለአንባቢያን ለማሳወቅ ፈቃድዎ ከሆነ ምስክርነትዎን በጽሑፍ ቢልኩልን በዚህች መጽሔት አማካኝነት ለብዙዎች በረከት ልናውለው እንችላለን።

## ማስታወቂያዎች




«የተስፋ ድምጽ» ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ
«ወንጌል የምሥራች ነው። የምሥራችም ደግሞ ደስታ»

ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ ጣቢያ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከጥቅምት ወር 1993 ዓ.ም. ጀምሮ ተስፋን የተሞሉ ፕሮግራሞቹን ይዞ በ 4 ቋንቋዎች በአየር ላይ ይገኛል። የስርጭቱ መስመርና ሰዓትም በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር እንደሚከተለው ነው፥

| ቋንቋ | ሠዓት | ሜትር ባንድ | SW ፍሪኩዌንሲ |
|---|---|---|---|
| አማርኛ | ጠዋት 12:00-12:30 | 25 | 15170 |
| አማርኛ | ምሽት 2፣00-2፣30 | 19 | 9515 |
| ኦሮምኛ | ምሽት 2:30-3:00 | 19 | 17560 |
| ትግርኛ | ጠዋት 12:00-12:30 | 25 | 15115 |
| ትግርኛ | ምሽት 2:30-3:00 | 19 | 15115 |



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

# የትንቢት ቃል

Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
Tel & Fax 0049 - 89 - 22 24 48
E-Mail: dawit.mehari@mail.com
E-Mail: dawitmengistu@web.de

ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ በየሶስት ወር ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ!
Sparkasse Nürnberg,
Yetnbit Kal,
Account Nr.: 3 516 113
BLZ: 760 501 01

***የተስፋፋው ተቃርኖ*** *(ከገጽ6 የዞረ)*

የበለጠ አደገኛ ነው። ሰዎችን ለማሳመን ብዙ ሀሰትን ከጥቂት እውነት ጋር መቀላቀል ሰይጣን ሰዎችን የሚያታልልበት መሳሪያው ነው። የእሁድ እንቅስቃሴ መሪዎች ሕዝቡ የሚፈልገውን የተሃድሶ እንቅስቃሴን እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማውን መሠረታዊ ትምህርት ሊያስተምሩ ይችላሉ፣ቢሆንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚቃወም መመሪያዎችን ስለሚያወጡ የጌታ ባሪያዎች ከነሱ ጋር መተባበር የለባቸውም። የሰዎችን ደንቦች (ወግ) ለመቀበል ሲባል የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚሻርበት አንዳችም በቂ ምክንያት የለም። ■

***<u>ይቀጥላል</u>***

## የጥያቄዎ መልስ

### «የሰማይ ቤታችን ምን ይመስላል?»

*ወ/ሮ መ.ኢ. ከዱልመን, ጀርመን*

ይህ ጥያቄ የብዙ ሰዎች ጥያቄ ነው። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ በጥቂቱ ነው መልስን የሚሰጠን። ለዚያውም በዚያ ያለውን ክብር በቃል ለመግለጽና በዚህ በተወሰነ አእምሮ ለመረዳትም ስለማይቻል በምሳሌያው አነጋገር ነው የሚያሳየን። ሐዋሪያው ዮሐንስ በራእይ ወደ ሰማይ ሲነጠቅ አተኩሮው በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ነበር (ራእይ 4፥1)። በዚያም ያየውንና የሰማውን በምሳሌያዊ አነጋገር ሲገልጽ ይታያል። ለምሳሌ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ስላሉት አራት ኪሩቤሎች (በቁ.7 ላይ ያሉት መላእክት) የገለጸውን አገላለጽ ቃል በቃል መወሰድ የለብንም። እነዚህ መላእክት ያላቸውን ባህርይ ግልጽ ለማድረግ ሲል ነው ይህንን ያለው (ክብራቸውን፣ኃያልነታቸውን፣አዋቂነታቸውን፣...)። በዙፋኑ አካባቢ ስላሉት ነገሮች ግን ዮሐንስ ብዙም አልጻፈም። ልቡ በእግዚአብሔር ክብርና በዙሪያው ባሉት መላእክት ከመማረኩ የተነሳ ሌላ ነገር ለማየት ጊዜ ያገኘ አይመስልም። በቁ. 6 ላይ ስለሚያንጸባርቀው ብርሌ ስለሚመስለው የብርጭቆ ባህር እናነባለን። በአሁኑ ዘመን ቢኖር ኖሮ ዮሐንስ ይህንን እንዴት አድርጎ ይገልጸው ነበር? ምናልባት «የብርሃን ባህር» ይለው ይሆን? ሰማይ ለዮሐንስ የክብር ብርሃን የሞላበት ቦታ ነው።

የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚነግሩን የዳኑት አማኞች ዘለአለምን በሰማይ አይደለም የሚያሳልፉት። የሱስ ዳግም ሲመጣ ከእርሱ እና ከመላእክቱ ጋራ ወደ ሰማይ ይሄዳሉ። ከ 1000 አመታት በኋላ ከሰማይ ወደ ምድር ይመለሳሉ (ራእይ 20፥4 ና 21፥1-21)። ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ምድርን እንደ አዲስ ከፈጠራት በኋላ ነው። ዮሐንስ አዲሲቷን ምድር ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋና ምሳሌ ለመግለጽ ሞክሮአል እንደዚያም ቢሆን ግን ስለ አዲሲቱ ምድር ሲናገር አሁንም ትኩረቱ እግዚአብሔር በሚገኝባት በአዲሲቱ የሩሳሌም ላይ ነው።

ኢሳይያስ ራሱ ከረጅም ጊዜ በፊት ስለ አዲሲቷ ምድር ተናግሮ ነበር። በኢሳ 65፥17-25 እና 11፥6-9 ላይ በአዲሲቱዋ ምድር ስለሚኖረው ሕይወት ይገልጻል። በምእራፍ 65 ላይ ያሉትን ጥቅሶች ግን ብዙ ሰዎች በትክክሉ አልተረዱትም። ስለዚህ እነዚህን በአጭሩ ለመግለጽ እንሞክር፥ (ቁ. 20 ያንብቡ) ይህ ማለት በአዲሲቱ ምድር ሰዎች ይሞታሉ ማለት አይደለም። ምክንያቱም ሞት በዚያ አይኖርምና! ኢሳይያስ ለማለት የፈለገው፥ አንድ ሰው አሁን በምንኖርባት ምድር መቶ አመት ሁኖት በሚሞትበት ጊዜ በአዲሲቱ ምድር ይህ እድሜ ገና የሕጻን እድሜ እንደሆነ ማነጻጸሩ ነው። ለእስራኤሎች መቶ አመት መኖር እንደ ትልቅ በረከት ነበር የሚታየው፤ይህ እድሜ ግን ከዘላለም ሕይወት ጋር ሲነጻጸር እንደ ምንም ነው።

(ቁ. 23 ያንብቡ) ከጥቅሱ እንደምንረዳው በኢሳያስ ዘመን ብዙ ጊዜ ሕጻናቶች እንደተወለዱ ሳይሞቱ አልቀረም። ነብዩ በዚህ ጥቅስ ለመግለጽ የፈለገው መልእክት እንደዚህ አይነት መቅሰፍት (ማለት የሕጻናት ያለጊዜው መሞት) እንደማይኖር ነው። ኢሳይያስ በዚያው ምእራፍ መጨረሻ ላይ ስለ አዲሲቷ ገነት በአጭሩ ይገልጻል። አዎ አዲሲቷ ገነት ቀድሞ በኃጢያት ምክንያት እንዳጣናት አይነት ገነት ነው የምትሆነው። ስለዚህ አዲሲቷ ምድር በቃላት ለመግለጽ እስከሚያቅት ድረስ ውብ እንደሆነችና ምን እንደምትመስል በጥቂቱም ቢሆን ለማወቅ ስለ ቀድሞዋ ኤደን ገነት የተጻፈውን ያንብቡ (ዘፍ2)። በዚያም ሁላችንም የሚያስደስተንን ነገር ብቻ ነው የምናደርግ። ለምሳሌ ለእስራኤላውያን ቤት መስራትና የወይን እርሻ መንከባከብ በጣም አስፈላጊ ነገር ነበር፣ስለዚህ ያንን ያደርጉ ይሆናል። ሄንደል ለሚባለው የሙዚቃ ኮምፖኒስት ምናልባት የበለጠ የሚያስደስተው ነገር «ሃሌሉያ» የሚለውን የታወቀ ሙዚቃውን የሚያስንቅ ሰማያዊ ሙዚቃን መድረስና መጫወት ይሆናል።

በአዲሲቷ ምድር በጣም ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር እንኖራለን፣የሚያስደንቅ ተፈጥሮና ግሩም ፍጥረታት ባሉበት እንዲሁም የምታስደንቀዋ ዋና ከተማ ባለችባት ምድር እንኖራለን። ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው ግን ዮሐንስ በራእይ 21፥3 ላይ የተናገረው ነው፥ <u>እግዚአብሔር ለሁልጊዜ ከእኛ ጋር ይሆናል እኛንና እሱን የሚለያይ ነገር ከእንግዲህ አይኖርም።</u> ■

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com